Muharram 7, 1446 AH

ታላቁ የኢማን መንገድ



ዝግጅት፡ ናዲያ ቢያ

CamScanner

መግቢያ

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እና ባልደረቦቻቸው የ13 አመት የመካ ላዩ ስቃይ እና እንግልትን የሚቀይር ህልም ተመለከቱ! በህልማቸው ከመካ ተነስተው ልክ እንደ 'የማማህ' የተምር ዛፎች የሚበዙበትን ከተማ ሲገቡ ተመለከቱ። ያ ቦታ የስሪብ (መዲና) ነበር። አላህን በሰላም የሚገዙበትን አዲስ ማህበረሰብ በመፍጠር እስልምናን ከፍ ወደሚያደርጉበት መዲና እንዲሰደዱ ጌታዬ አዘዛቸው! ሂጅራ የኢማን መንገድ ነው።

ሒጅራ ትላቅ የታሪክ ክስተታችን ነው። በህይወታችን ብዙ ሂጅራዎች ያስፈልጉናል። ሂጅራ ማለት ከአንድ ነገር (ሀገር: ሰዎች) ተለይቶ መሄድ የሚለውን ያመለክተናል! አሁን ላይ ከሀገር መሰደድ ላይኖርብን ይችል ይሆናል፤ ከአንቶ ፈንቶ ወሬዎች ሂጅራ ማድረግ ግን አለብን። አደብ ከጎደላቸው ንግግሮች፤ ድፍረት ከተሞላባቸው አጀንዳዎች ሂጅራ ማድረግ ይኖርብናል። አዲስ ማህበረሰብና መንደር ለመፍጠር ላንገደድ እንችል ይሆናል የራሳችንን አለም፤ ሀሳባችን ከሚገባቸው እና መልካም ስራዎችን አብረን ከምንሰራቸው ሰዎች ጋር ፋሬያማ ስብስብ በመፍጠር ሒጅራ ማድረግ ግን እንችላለን።

هجرة النبي الى المدينة

CamScanner



ማውጫ

01 የመጀመሪያዎቹ ተጓዦች

02 የመስዋዕትነት ጉዞ

03 የሰዩዲና ኡመር ሒጅራ

04 የረሱል ﷺ ሒጅራ

05 በመንገዳቸው ላይ

06 ከኡሙ ማዕበድ ጋር

CamScanner

የመጀመሪያዎቹ ተጓዦች

ከሁለተኛው የአቀባ ስምምነት በኃላ አርሳቸውን በነፍሳቸውና ባላቸው ነገር ሁሉ ለመጠበቅ ቃል የገቡት የእንሳር ሰዎች ወደ የስሪብ (መዲና) ረሱለላህን ﷺ ለመቀበል በደስታና በጉጉት ተመለሱ! የለውጡ መንገድ መጠረግ የጀመረው የአቀባ ስምምነት ላይ ነበር።

አዲስ ፊቶች፤ አዲስ ቃልኪዳኖች፤ አዲስ ታሪክ! . . . . . بسم الله

ከስምምነቱ በኃላ ረሱለላህ ሰሐቦችን በድብቅ ሰበሰቡና እንዲህ አሏቸው! "አላህ ሒጅራ የምናደርግበትን ምድር በህልሜ አሳይቶኛል፤ ረጂድም የተምር ዛፎችና አሰተ-ጎመራ የወለዳቸው ድንጋዬች ያሉበት አካባቢ ነው።" አሏቸው! በመጀመሪያው ቦታው የት እንደሆነ አላወቁም ነበር ይለሱ እንዳንድ ሙሐዲሶች። ከዛ በቀጣየ "አላህ የስሪብ እንደሆነ አሳየኝ።" በማለት ይገልፁሉ።

ሰሐቦች ይህንን ከሰሙ በኃላ አንድም ሁለትም እየሆኑ በድብቅ ወደ መዲና ሒጅራ ማድረግ ጀመሩ! ይህንን ማድረግ የቻለው የመጀመሪያው ሙሐጂር አቡ ሰለማ رضي الله عنه ነበር። አቡ ሰለማ ከሚስቱ ኡሙ ሰለማ እና አንድ ልጁ ጋር በመሆን ወደ ሐበሻ ሒጅራ ካደረጉት መካከል ነበሩ። ከዛ ከተመለሱ በኃላ የመዲናውን ሒጅራ ሲሰሙ ጓዛቸውን አስተካከለው ጉዟቸውን ጀመሩ! አቡ ሰለማ የአረብ ጎሳ ቢሆንም ቁረይሺ አልነበረም። እሱን በመተማመን በግልፅ ሂጅራ ማድረግን ወስኖ ጉዞውን ጀመረ።

የዚህን ሰዓት የቁረይሽ ሰዎች መሀል መንገድ ላይ ያዟቸውና "አቡ ሰለማ ሆይ! ምን እያደረግክ ነው?" አሉት! አቡ ሰለማ ፡ም ፡ "እኔ የእናንተ ጎሳ አስካልሆንኩ ድረስ ነፃ ነኝ። ወደ የስሪብ እየሄድኩ ነው።" አሳቸው! እነርሱም ፡ "አዎ! አንተ እንኳን ቁረይሽ አይደለህም መሄድ ትችላለህ፤ ሚስትህና ልጁ ግን ያንተ ስላልሆኑ እነርሱን መውሰድ አትችልም።" ብለው ልጁንና ውድ ሚስቱን ቀሙት! ሙቡ ንብረቱን ወስደው ከከተማው አባረሩት።

የአቡ ሰለማ ጎሳዎች ይህንን ሲሰሙ ጀሊሊያቸው አብሪታቸውን ቀሰቀሰውና ተሰባስበው ቁረይሾች ጋር ሄዱ። እንደደረሱም ፡ "በእርግጥ አስዋ የእናንተ ጎሳ ስለሆነች ማቆየት ትችላላችሁ፤ ልጁ ግን የኛ ዘር ነውና ልጁን እንወስዳለን።" ብለው ወስደውት ሄዱ! ኡሙ ሰለማ ትናገራለች ፡ "ለ16 ወራቶች ልጇ ወዳለበት አካባቢ እየሄድኩ ከሩቁ እያየሁት አለቅሳለሁ፤ ለቅሶዬ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ያሳምመኝ ጀመር፤ የዚህን ጊዜ የአክስቴ ልጆች ትንሽ አዝነውልኝ ልጇን ለእናት እንዲመልሱ ይማፀኑልኝ ጀመር። ከብዙ ልመና በኃላ መልሰውልኝ።" ትላለች። ከዛ በኃላ ኡሙ ሰለማ ልጅዋን ይዛ፤ ያለምንም ጓዝ ብቻዋን አቡ ሰለማ ወዳለበት ዳሩ ሰላም (መዲና) ሒጅራዋን ጀመረች።

እንዲህ ትላለች ፡ "ተንዒም የሚባለው አካባቢ ስደርስ ኡስማን ኢብን ጠለሓ ፡ን አገኘሁት። በቁረይሾች ዘንድ በጣም የተከበረ ትሁት ሰው ነበር። ሲመለከተኝ ያለምንም ጓዝ ብቻዬን ልጇን ይዤ ነው ያለሁት፤ ከዚያም ብቻዬን ለምን እንደሆንኩኝ ጠየቀኝ፤ ሁኔታዬን ሳስረዳው ፡ ወላሂ! ይህንን ሁሉ መንገድ ብቻሽን እንድትሄጂ አልፈቅድም እኔ ነኝ የማደርስሽ።፡ አለኝ።" በማለት ሁኔታውን ትገልፃለች!

ኡስማን ኢብን ጠልሓ በሰዓቱ ሙስሊም አልነበረም ነገር ግን የኡሙ ሰለማ ብቻዋን መጓዝ ሰብዓዊ ባህሪውን አሳዘነው። ከመካ ጀምረው መዲና እስከሚደርሱ ድረስ መንገዱን ፊት ሆኖ እየመራት፤ ምሽት ሲሆን እስዋ ዛፍ ስር እርሱ ደግሞ ግመሉ አጠገብ እየተኛ መዲና አደረሳት! እቺ ምርጥ ሴት በኃላ ላይ የረሱለላህ ውድ ሚስት የምትሆን ሆነች። ኡስማን ኢብን ጠልሓ ፡ም የከዓባ ፡ን ቁልፍ ከሚይዙትና እስከ የውመል አኺር ድረስ የእርሱ ዘሮች እሱን የሚያስቀጥሉበት ሰው ሆነ!

ኡሙ ሰለማ ከብዙ ወራቶች መቆራረጥ በኃላ ውድ ባለቤትዋን አቡ ሰለማን መዲና ላይ ተቀላቀለች!
ሒጅራ በእርግጥም የለውጥ ጉዞ ነው።

የመስዋዕትነት ጉዞ

ወደ መዲና ሒጅራ የማድረግ ዜናው ከደረሰ ጀምሮ ሰሐቦች መጓዝ ጀምረዋል። ሐቢበላህ አሁንም መካ ውስጥ ናቸው! የመጀመሪያዎቹ ሙሐጂሮች ሲነሱ አንድ በብዛት ተያይዞ የሚነሳው ሰሐቢይ ሱሐይብ አር-ሩሚ رضي الله عنه ነበር።

ሱሐይብ ከሰሜናዊው የአረቢያን ምድር ከሆነው ጎሳ ነበር። ሮሞች ሀገራቸውን የተቆጣጠሩ ሰዓት ሮም ላይ አደገ፤ከዚያም በባሪያነት ወደ መካ ተሸጠ። በዚያ የጃሂሊያ ወቅት አንድ ባሪያ ሰርቶ ሰብስቦ በያዘው ገንዘብ አራሱን ነፃ ማውጣት ይችል ነበር። በዚህም ምክንያት ሱሐይብ ነፃ ሰው ሆነ! አነስ ያሰ ንግድም ከፍቶ መካ ላይ መንቀሳቀስ ጀመረ።

ረሱለላህ ﷺ የአስልምናን መልዕክት ሲቀበሉ በአማር ኢብን ያሲር አማካኝነት መጀመሪያ ላይ ከሰለሙት ሙስሊሞች መካከል መሆንም ቻለ። የሒጅራው ዜና ሲመጣ ከመጀመሪያዎቹ ተጓዦች በመሆን መንገዱን ጀመረ!

መካውያን ስለ ሙስሊሞች አንድም ዜና አያመልጣቻውም ነበርና ይህንን ሲሰሙ ውስን የሆኑ ወታደሮቻቸውን ሱሐይብን ከከተማው ውጪ ሆነው ጠብቀው እንዲይዙት ይልካሉ። ሱሐይብ ገና ከመካ እንደወጣ ወታደሮቹ ከበቡት! በዚህ ቅፅበት ሱሐይብ በአጂ ይዞት የነበረውን ቀስት እና ደጋኑን አወጣና: "እናንተ የቁረይሽ ሰዎች ሆይ! አርባ የሚጠጋ ቀስት ጊዜ ውስጥ ይዣለሁ። በአላህ እምላለሁ! አያንዳንዱን ቀስቶቼን ሳልጠቀም ማናችሁም ወደ እኔ አትጠጉም። እንደዛም ሆነ አሁንም ወደ እኔ የምትጠጉ ከሆነ በያዝኩት ጎራዴ አስተናግዳችኃለው። ከመንገዴ ላይ የሚያስቆመኝ አንዱንም አካል ምህረት አላደርግለትም።" በማለት ተናገረ

የመጡት ወታደሮች ሱሐይብን ሊያስቆሙት ቢፈልጉም ሱሐይብ የነበረው ሐይልና ቆራጥነት ግን ለነፍሳቸው እንዲፈሩ አደረጋቸው። ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግር ብሏቸው ማሰብ ጀመሩ! ማን ቀድሞ ያጠቃል ብለው እያሰቡ ባለበት ሱሐይብ እንዲህ አለ:

"አስከዛሬ ያካበትኩትን ሐብት በሙሉ የደበቅኩበትን ቦታ ብነግራችሁ እንድሄድ ትፈቅዱልኛላችሁ?" ብሎ አሳቸው። ወታደሮቹ ያሰምንም ማንገራገር አዎ አሉ። ሱሐይብ ' ም ሐብቱ ያለበትን ቦታ ጠቁሚቸው በለበሰው ልብስ ብቻ ከባርነት ነፃ ከሆነ ጀምሮ ያካበተውን ሀብት ለአላህና ለመልዕክተኛው ﷺ ውዴታ ሲል መስዋዕት አደረገ! አዲስ ህይወትን ለመጀመር ሲባል፤ አዲስ ምዕራፍን ለመኖር ወደ ምርጧ ምድር መዲና ዘለቀ።

በኃላ ላይ ረሱለላህ ሱሐይብን ሲያገኙት እንዲህ አሉ: "ያ ሱሐይብ! አላህ ባንተ ምክንያት አኮ አያህን አወረደ። "ربح البيعي أبا يحيى" :አባ የህያ ሆይ! በአርግጥ ሽያጭህ ስኬታማ ነበር።" አሉት!

وَمِنَ النَّاسِ مَن يَشْرِي نَفْسَهُ ابْتِغَاءَ مَرْضَاتِ اللَّهِ وَاللَّهُ رَءُوفٌ بِالْعِبَادِ

"ከሰዎችም ውስጥ የአላህን ውዴታ ለመፈለግ ነፍሱን የሚሸጥ ሰው አልለ። አላህም ለባሮቹ በጣም ርኅሩህ ነው።" [ሱረቱል በቀራህ: 207] . . . .ይህ ምርጥ አያህ በሱሐይብ አርሩሚ ምክንያት ወረደ!

ሒጅራ ለማድረግ ዱንያውን ሸጠ። የነፍሲያውን ንፍገት ስላስጠበቀ አኺራውን ሸመተ። ከባርነት ነፃ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ያካበተው ንብረት የአላህን ውዴታ የሚያስገኘው አስከሆነ ድረስ ድርድር ውስጥ ለመከተት ለአፍታም አላንገራገረም ነበር። የመጨረሻዬቱ አለም በአርግጥ ከቅርቢቱ ዓለም እንደምትበልጥ ጠንቅቆ ተረድቷል። አርሱም ኖሮታል

ምን ያማረ ሽያጭ! ምን ያማረ ሒጅራ!

የሰይዲና ኡመር ሒጅራ

ሰዩዲና አሊዩ ኢብን አቢ ጧሊብ: "እንደ ኡመር ሒጅራውን ዩፋ አድርጎ ጉዞ የደረገ ሰው አላውቅም።" ዩሳሉ! . . . ኡመር ኢብኑል ኸጣብ رضي الله عنه ከቤተሰቦቻቸው ጋር ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት ትጥቃቸውን አሟልተው፤ ጓዛቸውን ሸክፈው ወደ ከዓባ አቀኑ። የስንብት ጠዋፋቸውን የመካ ሹማምቶች እየተመለከትዋቸው አደረጉ። ረከዓተይን ከሰገዱ በኃላ ወደ ቁረይሽ ህዝቦች ዞር ብለው እንዲህ አሉ:

"ዛሬ እናቱ እንድታጣው የሚፈልግ ሰው ካለ፤ ልጆቹ የቲም እንዲሆኑበት የሚሻ ሰው ካለ ብሎም ሚስቱ ባሏ የሞተባት ሴት እንድትሆን የሚፈልግ ሰው ካለ እኔ ወደ መዲና ሒጅራ እየደረግኩ እንደሆነ ዩወቅ! ዩህንን የሚሻ ሰው የመካ ዳርቻ የሆነው ቦታ ላዩ ሊያገኘኝ ዩችላል።" በማለት ጀግናው ኡመር ሒጅራቸውን ዩፋ አደረጉ! ሱብሓነላህ

ያ ኡመር! . . . ለዛም ነው የሰዩዲና ኡመር መስለም የሙስሊሞች መጠናከር ላዩ ትልቅ ተፅዕኖ የፈጠረው፤ ለዛም ነው ሸፊዒ በኡመር ምክንያት ዲኑ እንዲጠናከር በጥብቅ ዱዓ ያደረጉለት! ሰዩዲና ኡመር እስልምናን ሲቀበሉ እኮ ጂብሪል ወደ ረሱለላህ ﷺ መጣና እንዲህ አላቸው።

« يا محمد، لقد استبشر أهل السماء بإسلام عمر

"ያ ሙሐመድ ﷺ! ኡመር በመስለሙ ምክንያት እኮ ሰማዩ ውስጥ ያሉ ነዋሪዋች (መላዒካዎች) ደስታውን እያከበሩ ነው።" አላቸው! የኡመር መስለም ሰውንም መላዒካውንም እጅግ አስደስቶ ነበር።

አብዱላህ ኢብን መስዑድ ደግሞ እንዲህ ዩላሉ:

إن إسلام عمر كان فتحا ، وإن هجرته كانت نصرا ، وإن إمارته كانت رحمة

"ወለላ! የኡመር መስለም በራሱ ፈትሕ ነበር፤ ሒጅራው ደግሞ ድል ነበር፤ አመራሩ ደግሞ ራህማ ነበር።" ዩላል። ምን አዩነት ድንቅ ገለዓ ነው!

ሰዩዲና ኡመር ሒጅራ ሊያደርጉ ሲሉ ከራሳቸው ጋር ሁለት ሴሎች ሰሐቦችን መርጠው ነበር። አንደኛው የአምር ኢብን አስ ወንድም ሒሻም ኢብን አስ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ከአቡጀሕል ጋር በአናት አንድ ከሆኑት ወንድሙ አያሽ ኢብን አቢ ረቢዓ ጋር ሊጓዙ ወሰኑ። የሚገናኙበትን ቦታ ወስነው ተቀጣጠሩ! በቀጠሯቸው ቀን ግን የተገኘው አያሽ ብቻ ስለነበር ከአርሱ ጋር ሒጅራ ማድረግን ጀመሩ። ሒሻም በተቀጣጠሩበት ቦታ ያልተገኘው በቁረይሾች ተዩዘ ስለነበር ነበር።

ቁረይሾች የሰዩዲና ኡመር ' ን ጀግንነት ያውቁ ስለነበር አንድም ሰው ከጉዟቸው ሊያሰናክላቸው አልሞከረም። በሰላም ወደ መዲና ዘለቁ! አቡ ጀሐል ግን አዩኑ አያየ ወንድሙ ከኡመር ጋር ሒጅራ ሲያደርግ ምንም ማድረግ አለመቻሉ አረፍት ስላልሰጠው በትንሽ ቀናት ልዩነት ውስጥ ወደ መዲና ሴራ በመጎንጎን ያቀናል። ወደ ወንድሙ አያሽ በመሄድም እንዲህ አለው።

"ወንድሜ ሆዩ! አንተ አዚህ ከመጣህ በኃላ አናታችን ምግብ በልታ፤ ውሃ ጠጥታ አታውቅም። ፀጉሯንም ታጥባና ተበጥራ አታውቅም፤ አንተ መጥተህ ካላፅናናሃት በስተቀር በህዩወት የምትቆዩ አዩመስለኝም።" አለ አቡጀህል የሴራ መረቡን ሲዘረጋ! . . .እናት አናት ናትና አያሽ ልቡ አዘነ፤ አንድ አፍታ አዩቷት ለመመለስም ወሰነ። ወደ ሰዩዲና ኡመር በመሄድ አቡጀሐል የነገረውን ከነገረው በኃላ ወደ መካ ሊመለስ እንደሆነም አጫወተው።

ኡመር የአቡጀሕል ንግግር የሴራ አንደሆነ ስለገባው አያሽን ወንድሙ አየዋሸው አንደሆነ ዩነግረዋል። አያሽ ግን አላስቻለውም ወደ መካ ሊመለስ ሆነ። የዚህን ጊዜ ሰዩዲና ኡመር ወዳጃቸው አያሽን ጠሩትና አንዲህ አሉት : "አያሽ ሆዩ! እንግዲያውስ መሄድህ ግድ ከሆነ የኔን ግመል ዩዘህ ሂድ። የኔ ግመል ከአነርሱ ግመል የተሻለ ፍጥነት ስላለት መንገድህ ላይ የሚያጠራጥር ነገር ከተመለከትክ ቶሎ ወደ መዲና መመለስ ያስችልሃል።" ብሎ ሰጠው። በደም አንድ ከሆነው ወንድሙ በላይ በአስልምና ገመድ የተሳሰረው ወንድሙ ለአያሽ ደህንነት አሰበ! ያ ኡመር

አያሽ ሒድራ ከማድረጉ በትንሽ ቀናቶች ልዩነት ወደ መካ መመለስ ጀመረ። አቡጀሕል ግን ሴራዎች የማያልቁበት ሰው ነውና መሐል መንገድ ሲደርሱ የአርሱ ግመል መንቀሳቀስ አንዳቃታትና በአያሽ ግመል ሆነው አንዲሄዱ ዩጠዩቀዋል። አያሽ ሳሰቡ አልገባውም ግመሱ አንድትቀመጥ ሲያደርግ ወዲያው አቡ ጀሐል አጁን ያስረዋል። አንዳሰረውም ሀዩሱን ለማሳየት መካ ውስጥ አያዞረው : "ሞኙትን በዚህ መልክ ነው የምናስተናግደው።" አያለ ህዝቦቹን ያሳዩ ነበር። አስቡት ዩህ ሲፈጠር ረሱለላህ ﷺ አና ውስን ሰሐቦች ገና ወደ መዲና ሒድራ አላደረጉም ነበር።

በተመሰሰዩ ሰዓት መዲና ላዩ አንሷሮችና ሙሐጂሮች አንድ ላዩ በመሆን የረሱለላህን ﷺ መምጣት ዩጠባበቃሉ! ነፍሳቸውን ጭምር መስዋዕት ሊያደርጉላቸው የሚፈልጉ ወዳጆቻቸው የናፈቅዋቸውን ነብዩ ﷺ ለመቀበል ዝግጅት ላዩ ናቸው። . . . የከውኑን ተጨባጭ የቀየረው የረሱሉ ﷺ ሒድራ እንዴት ነበር?

የረሱሊ ﷺ ሒጅራ

አብዘሃኞቹ የመካ ሙስሊሞች ወደ መዲና ሒጅራ አድርገዋል። አሁን ላይ የቀሩት ሸፊዒ ﷺ፤ ሰዩዲና አባበክርና ቤተሰቦቻቸው፤ ሰዩዲና አሊዩ እና አንዳንድ ሴቶችና ህፃናቶች ብቻ ነበር።

አንድ ለሊት ላይ ረሱለላህ ﷺ ወደ አባበክር ቤት ድንገት ይመጣሉ። ማንም ስለዚህ ጉዳይ መስማት የለበትም ሲሏቸው ልጇ አሚሻ እና አስማ ብቻ ናቸው ያሉት አሱ አባበክር። ከዛም ሸፊኢ ﷺ ወደ መዲና ሂጅራ እንዳደርግ ታዝዤያለው ሲሏቸው አፍቃሪያቸው አባበክር ወዲያውኑ፡ "አሱህባ ያ ረሱለላህ?፡ ባልደረባነቶ'ን ያ ረሱለላህ ﷺ" አሉ። የዚህን ጊዜ "አዎ አንተ ነህ የጉዞ ባልደረባዬ ብለው አስደሰቷቸው።"

አባበክር በደስታ ብዛት ተፍለቅልቀው አለቀሱ! አናታችን አሚሻ፡ "በደስታ ብዛት ሲያለቅስ የተመለከትኩት አባቴን ብቻ ነው።" በማለት ሁኔታውን ትገልጻለች። ወዲያውም ለጉዞ ሁለት ግመል አዘጋጁ! ታላቅ ልጃቸው አስማ በቆይታቸው ምግብ እንድታቃብላቸው፤ ልጃቸው አብደላህ መካ ላይ ያለውን ዜና አድምጦ እንዲያደርሳቸው፤ አምር ኢብን ፉኸይራ የሚባል ነፃ ያወጡት ባሪያ ደግሞ መንገድ ጠቋሚያቸው እና አየተከታተለ ኮቴያቸውን እንዲያጠፋ መደቡት።

ግን አላህ ከብዙ ለሊቶች ይህንን ለሊት ሒጅራ እንዲያደርጉ ለምን መረጠላቸው? ምክንያቱም በዚያ ለሊት የቁረይሽ ጎሳዎች በሙሉ በኑ ሐሺሞችን ብቻ ሳያካትቱ 'ዳሩ ነድዋ' በሚባል ቦታ ላይ የድብቅ ስብሰባ አድርገው ነበር። አጀንዳው የረሱለላህ ﷺ ጉዳይ ነው፤ አጎታቸው አቡ ለሐብ'ን እንኳን ያካተተ አልነበረም። አቡ ለሃብ የቱንም ያህል ከፋ ሰው ቢሆን የወንድሙን ልጅ ግ*ድያ ላይ ግን እንደማይተባበር እርግጠኛ ስለሆኑ ከስብሰባው ውጪ አደረጉት!

ምክክራቸውንም ጀመሩ። በዚህ መሐል አንድ ሽምገል ያለ ሰውዬ ወደ ስብሰባው ቦታ ይመጣል፤ ፊቱ አዲስ ስለሆነባቸው ከየትኛው ጎሳ እንደመጣ ይጠይቀታል። ከነጅድ እንደመጣ፤ አጀንዳው ስለ ረሱለላህ ﷺ እንደሆነ ደርሶት ሊቀላቀላቸው እንደመጣ ነገራቸው! እርሱም ስብሰባቸውን ተቀላቀላቸው። ሽማግሌው ኢብሊስ ነበር።

ከዚያም አሳቸውን ምን ማድረግ እንዳለባቸው መነጋገር ጀመሩ። እንደኛቸው፡ "ቤት ውስጥ አንድ ቦታ ላይ ብናስረው'ስ?" አለ። ኢብሊስ የዚህን ሰዓት፡ "ካሰርነው'ማ እርሱ አሁን ከአምላክ አየወረደልኝ ነው የሚለውን ንግግር ለተከታዬቹ ማድረሱ አይቀርም።" አለ። ከዚያ ደግሞ እንደኛቸው፡ "እሺ ከመካ ብናባረው'ስ?" አለ። ሽማግሌው ሰውዬ (ኢብሊስ) ወዲያው፡ "ይህ ማለት እኮ ወደ ተከታዬቹ ሒጅራ ወዳረጉት መሳክ ማለት ነው።" አለ!

መጨረሻ ላይ ሁሉም ልብ ውስጥ ያለውን ነገርግን ለመናገር ያልደፈሩትን ሀሳብ አቡ ጀሐል አነሳ፡ "ታዲያ ለምን አንገ*ድለውም? ነገር ግን አንድ ጎሳ ብቻ ተጠያቂ መሆን ስለሌለበት የሁላችንም እጅ ይኖርበታል። የዚህን ጊዜ በኑ ሀሺሞች ዲያዕ (የደም ክፍያ) መጠየቅ ይችገራሉ" አለ።

ኢብሊስ የሚፈልገው ነጥብ ላይ ሲደርሱለት፡ "አዎ! ይህ ነው ትክክለኛው ውሳኔ!" አላቸው። ከዚያም ለግድ*ያው መዘጋጀት ጀመሩ! ይህንን ምክክር እያደረጉ ባለበት ሁኔታ ላይ አላህ ጂብሪልን በመላክ ምን እያቀዱለት እንደሆነ ይነግራቸዋል። ረቢ ይህንን ከስተት ሱረቱል አንፋል ላይ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል።

وَإِذْ يَمْكُرُ بِكَ الَّذِينَ كَفَرُوا لِيُثْبِتُوكَ أَوْ يَقْتُلُوكَ أَوْ يُخْرِجُوكَ وَيَمْكُرُونَ وَيَمْكُرُ اللَّهُ وَاللَّهُ خَيْرُ الْمَاكِرِينَ

"እነዚያም የካዱት ሊያስሩህ ወይም ሊገድሉህ ወይም (ከመካ) ሊያወጡህ ባንተ ላይ በመከሩብህ ጊዜ (አስታውስ)። ይመክራሉም አላህም ተንኮላቸውን ይመልስባቸዋል። አላህም ከመካሪዎቹ ሁሉ በላይ ነው።" . . .

አላህ በአርግጥም ከመካሪዎቹ ሁሉ በላዩ ነው! እነሱ ቢያሴሩም ሐቢበላህ ' ን ﷺ የሚጠብቀው ጌታ ተንከላቸውን መለሰባቸው። ሒጅራውን ከአባበክር ጋር ከተነጋገሩ በኃላ ቁረይሾች ከየጎሳው የተውጣጡ ሰዎችን ወደሳቸው ቤት በለሊቱ ላኩ። የዚህን ጊዜ ሐቢበላህ ﷺ ሱረቱል ያሲን ላይ ያለውን አያህ መቅራት ጀመሩ።

وَجَعَلْنَا مِن بَيْنِ أَيْدِيهِمْ سَدًّا وَمِنْ خَلْفِهِمْ سَدًّا فَأَغْشَيْنَاهُمْ فَهُمْ لَا يُبْصِرُونَ

"ከስተፊታቸውም ግርዶን ከስተኋላቸውም ግርዶን አደረግን። ሸፈንናቸውም። ስለዚህ እነሱ አያዩም።"
[ሱረቱል ያሲን:9]

አላህ ሐቢበላህን ﷺ እንዳዩመለከቷቸው አደረገ። ሸፈናቸውም ሱብሃነላህ! ከዚያም በዚሁ ለሊት ወደ አባበክር ጋር ጉዟቸውን ጀመሩ! ዩህንን ከማድረጋቸው በፊት ግን ለአንድ ወዳጃቸው ትልቅ የቤት ስራን ሰጡ! ሰዩዲና አሊዩ ' ን በአሳቸው ፋንታ አልጋቸው ላዩ እንዲተኛ ጠየቁት።

አፍቃሪያቸው አሊዩ ዩህንን ጥያቄ ለመቀበል ሰከንዶችን አላንገራገረም ነበር። ህዩወቱን ሊያጣበት የሚችልበትን ከባድ የቤት ስራ ከህዩወታቸው በላዩ ለሚወዳቸው ሙስጠፋ ብሎ በደስታ ተቀበለ። ሁሉም ሰሐቢዩ ረሱሊ ' ን ﷺ ሊቀበል ቀድሞ ሲሰደድ አሊዩ ለአሳቸው ቤዛ መሆንን አስበለጠ። የውዱ አልጋ ላዩ ' ም ጋደም አለ። "እንደዛ ቀን ሰላማዊ እንቅልፍ ተኝቼ አላውቅም።" ዩላሉ አሊዩ ሱብሃነከ ⊠⊠

በጠዋቱ የመካ ሙሽሪኮች እንደ ሴራቸው ሊፈፅሙ ሲገቡ በረሱል ﷺ ፈንታ አሊዩ ' ን አገኙት፤ መሸወዳቸውን ሲያስተውሉ መግ*ደል ዩችሉ ነበር አላህ ግን ድጋሚ ከሚያፈቅሩትና ከሚያፈቅሯቸው መልዕክተኛ ﷺ ጋር እንዲቀላቀል ስለፈቀደ ሴራቸውን አከሸፈባቸው። አላህ ላዩ የነበረው መተማመን ምንም እንዳያደርጉት ጠበቀው! ⊠

ሐቢበላህ ﷺ ከወዳጃቸው አባበክር ጋር ሆነው ከመካ እንደወጡ አስከሚመለሱ ድረስ የሚናፍቁትን ሀገራቸውን ዞር ብለው ተመለከቱና: "መካ ሆዩ! አለም ላዩ በጣም ተወዳጅ ከሆኑት ቦታዎች መካከል ነሽ፤ ለኔም ተወዳጅ ነሽ። ህዝቦቼ ከሀገሬ ባያባሩኝ ኖሮ ጥዬሽ ባልወጣው ነበር።" አሉ! ከዚያም ዱአ አድርገው መንገዳቸውን ቀጠሉ! ⊠

ወደ መዲና የሚወስደውን ዋናውን መንገድ ትተው ወደ ' ጋሩ ሰውር ' ዋሻ የሚወስደውን መንገድ መርጠው መጓዝ ጀመሩ። ሶስት ቀን እና ለሊቶች አዛ ሆነው ሊጠባበቁ ወደ ዋሻው ዘለቁ። የዚህን ሰዓት አምር ኢብን ፉኸይራ የአባበክር ልጅ አብደላህ መካ ሌዶ ዜናውን ሰብስቦ ወደ ዋሻው ሲመጣ፤ እንዲሁም አስማ ስንቅ ስታቃብላቸው እየተከታተለ የአግር ኮቴያቸውን ያጠፋ ነበር።

ረሱለላህ ﷺ ከዋሻው ባልደረባቸው ጋር አዛች ጠባብ ዋሻ ውስጥ ተቀመጡ። በዚህ ሰዓት የቁረይሽ ሹማምንቶች ረሱለላህን ﷺ እና ባልደረባውን ያገኘ ሰው 100 ግመል ይሸለማል ብለው አዋጅ ስላወጡ ሰዎች ሁሉ አሳቸውን ፍለጋ ላዩ ናቸው።

ነቢየላህ ﷺ ዋሻው ውስጥ የነበራቸው ቆዩታና ከዋሻው ከወጡ በኃላ በመንገዳቸው ላዩ ምን ገጠማቸው?

በመንገዳቸው ላይ

መንገድ እንደጀመሩ አባበክር ግር የሚል ነገር ማድረግ ጀመሩ። እንዴ ከረሱሊ ይርባ፤ እንዴ ከፊት ለፊታቸው፤ እንዴ ከጎናቸው በመሆን ይራመዳሉ። ይህን ጊዜ ሸፊዒ ﷺ ግራ ገብቷቸው "የ አባበክር ምን ነካህ?" አሉት። ባልደረባቸውም "ድንገት ሰዎች አርሶን ለያጠቃዎት ቢመጡ እንዴት መከላከል እንዳሰብኽ ለማየት ነው አሏቸው!" አወይ የፍቅር ነገር!

እንኳን ሁለት ሰው እንድ ሰው እንኳን ለማስገባት በጣም የሚያስቸግረው ዋሻው ውስጥ ገቡ። እንደገቡም ሐቢቢ ﷺ እንቅልፍ ወሰዳቸው፤ ትንሽ ሳይቀየም አባበክር በአባብ ተነደፋ፤ አሚቸዋል ነገር ግን ውዱ መልዕክተኛቸውን ሳለመረበሽ ህመማቸውን እንደምንም ለመቻል ሞከሩ። ለፍቅራቸው ሲሉ ቻሉት! እንባቸው ግን አልቻለም። የእንባቸው ዘለላ የዘዩኔ ﷺ ገላ ላይ አረፈ! ሸፊዒ ﷺ በእንባቸው ምክንያት ከእንቅልፋቸው ነቁ። አባበክር የተነደፈበትን ቦታ ዱኣ አደረጉበት። አላህ ' ም በትሮታው አዳናቸው!

ሰዩዲና አባበክር ከዋሻው ከወጡ በኃላ ወደ መዲና የሚወስዳቸው አብደላህ ኢብን አርቀት የሚባል ከቁረይሾች ያልሆነ መንገድ ጠቋሚ አዘጋጅተው ነበር። ቦታቸው እንዳይገኝ ብዙ አቅድ ቢያቅዱም የቁረይሽ ሹማምንቶች አለ የተባለ ጎበዝ ሰላዩ መደቡ። የአበበክር ግመል የት ሊሄድ እንደሚችል እንዲያጣራ ቀጠሩት! ሰላዩ በጣም ጎበዝ ስለነበር ልክ እንደ አባጀህል፤ አል ወሊድ ኢብን ሙጊራ እና ሌሎች ውስን የቁረይሽ ሙሽሪኮችን አስከትሎ ጋሩ ሰውር ድረስ መራቸው! የዚህን ሰዓት አባበክር ደነገጡ። "የ ረሱለላህﷺ! በያዩን ' ስ?" አሉ

ሲዲቁ ሐቢቢ ﷺ የሆነ ነገር እንዳይሆኑ በሚል ፍርሃት እና ጭንቀት ይንቀጠቀጡ ጀመር። ሸፊዒም ﷺ ባልደረባቸውን አረጋጉትና እንዲህ አሉት :

يا أبا بكرٍ ما ظَنُّكَ باثنينِ اللهُ ثالثُهُما
"አባበክር ሆዩ! ሶስተኛቸው አላህ ስለሆኑላቸው ሁለት ሰዎች ምን ትላለህ?" አሉት።

አላህ ከነሱ ጋር እንደሆነ በመንገር ለያረጋግዋቸው ሞከሩ፤ አየዳበሷቸውም "የ አባበክር! ላ ታህዘን ኢነላሃ ማዕና!" አሉት። . .አላህም ይህንን የፍቅር ትዕዩንት በዚህ መልክ ቁርኣኑ ላይ ይገልፀዋል :

إِلَّا تَنصُرُوهُ فَقَدْ نَصَرَهُ اللَّهُ إِذْ أَخْرَجَهُ الَّذِينَ كَفَرُوا ثَانِيَ اثْنَيْنِ إِذْ هُمَا فِي الْغَارِ إِذْ يَقُولُ لِصَاحِبِهِ لَا تَحْزَنْ إِنَّ اللَّهَ مَعَنَا فَأَنزَلَ اللَّهُ سَكِينَتَهُ عَلَيْهِ وَأَيَّدَهُ بِجُنُودٍ لَّمْ تَرَوْهَا وَجَعَلَ كَلِمَةَ الَّذِينَ كَفَرُوا السُّفْلَىٰ وَكَلِمَةُ اللَّهِ هِيَ الْعُلْيَا وَاللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ

"(ነቢዩን) ባትረዱት አነዚያ የካዱት ሕዝቦች የሁለት (ሰዎች) ሁለተኛ ኾኖ (ከመካ) ባወጡት ጊዜ አላህ በእርግጥ ረድቶታል። ሁለቱም በዋሻው ሰቡ ለጓደኛው አትዘን አላህ ከእኛ ጋር ነውና ባለ ጊዜ አላህም መረጋጋትን በእርሱ ላይ አወረደ። ባላያችኋቸውም ሰራዊት አበረታው።"

ሱብሃነላህ! ይህንን ክስተት ደግሞ ደጋግሞ መስማቱ እራሱ አያስጠግብም። ሰዩዲና አባበክር ለሐቢቢ ያላቸውን ፍቅር መሰል የሚሰጠው ስሜት እራሱ ቀላል አይደለም!

አላህ በድጋሚ ከሙሽሪኮቹ ጠብቋቸው ከዋሻው ወጡ። ከአብደላህ ኢብን አርቀት ጋር የተቀጣጠሩበት ቦታ ተገናኝተው ጉዟቸውን ቀጠሉ! በዚህ መሃል ስንቅ ከምታቀብላቸው አስማ ጋርና ከአባበክር ልጅ ጋር መንገድ ላይ ተጠፋፋተዋል! በሆንም መንገዳቸውን ቀጠሉ።

አየተጓዙ መንገዳቸው ላይ ጁዕሽም የሚባል የጎሳ መሪና ተከታዮቻቸውን አገኙ። ሱራቃ ኢብን ማሊክ ይባላል። ከበደዊኖቹ ነበር! ሱራቃ እንዲህ በማለት የተፈጠረውን ይናገራል:

"ከተከታዬቼ ጋር ተቀምጬ ባለበት ሶስት ተጓዦችን ያገኘ መቶ ግመል ይሸለማል የሚለው ዜና ደርሶኝ ስለነበር ሶስቱ ሰዎች ወደኛ አቅጣጫ ሲመጡ ከሩቁ አዩቼ ቁረይሾች የሚፈልጓቸው ሰዎች እንደሆኑ አወቅኩኝና ገንዘቡን የራሴ ለማድረግ ወደ እነሱ መገስገስ ጀመርኩኝ። ታጥቄ ወደ እነርሱ ለመቅረብና ለመያዝ ሞከርኩኝ። አየተጠጋሁ ስመጣ ግን በእኔና በእነርሱ መካከል ከበድ ባለ ጭስ ተሸፈነ! ግራ ገብቶኝ በያዝኩት ነገር ፊቴን የጋረደውን ጭስ ላጠፋ ሞከርኩኝ። በዚህ መሃል እንዳልጠጋቸው የሚያስጠነቅቀኝን ድምፅ ሰማሁ። እሁንም ለመጠጋት ሞከርኩ ድምፁ እሁንም ጆሮዬ ላይ አቃጨለብኝ። የዚህ ጊዜ ይህን ሰው እና ባልደረቦቹን የሚጠብቅ ሐይል እንዳለ ተረዳሁኝ። ከዛም ምንም አይነት ጥቃት እንደማላደርስባቸውና ሰላማዊ ሰው እንደሆንኩኝ አበሰርኳቸው። ከዚያም የጋረደኝ መጋረጃ ተገለጠልኝ።

. . . ስመለከታቸው እንደኖቸው አቅጣጫውን እየቀያየረ ይራመዳል፤ ከአንድ ሰው ጀርባ አንዴ ከፊት፤ አንዴ ከኋላ እየሆነ ይራመዳል። ከመሀከላቸው አንድ ሰው ደግሞ ፊቱ ያበራ ነበር። ረጋ ብሎ በምላሱ የሆነ ነገር እያነበነበ ይራመድ ነበር።" በማለት ክስተቱን ይናገራል።

ሱራቃ ወደእነርሱ ጋር ከተጠጋ በኃላ ረሱለላህ ﷺ በኃላ ላይ ሲያገኙት በምንም አይነት ሁኔታ ላይ ቢሆን ጥበቃውን እንዲሰጣቸው ቃል እንዲገቡለት ጠየቀ። ሸፊዒ ' ም ቃል ገቡለት። . . . መንገዳቸውን ከመቀጠላቸው በፊት ሱራቃ ተከታዮቹ ምግብ እንዲያቀርቡላቸው ጠየቀ። የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ግን አሻፈረኝ ብለው ጉዟቸውን ቀጠሉ።

አሱን ለሊት ካሳለፉ በኃላ በነጋታው አሁንም በመንገዳቸው ላይ አንድን ቤት ይመለከታሉ። በዚህ ሰዓት ግን እጃቸው ላይ ያለውን ስንቅ ስለጨረሱ ተርበዋል። የሚበላ ወይንም የሚጠጣ ነገር ካለ ለመጠየቅ ወደ ቤቱ ጎራ አሉ።

ቤቱ የበኑ ኹዛዓ ጎሳ የሆኑት ኡሙ ማዕበድ (ትክክለኛ ስምዋ: አቲካ ቢንት ኻሊድ አል ኹዛዒያ) እና የአቡ ማዕበድ ነበር። በሰአቱ እጅግ ከባድ በሆነ ድርቅ እየማቀቁ ነበር። ባልዋ አቡ ማዕበድ ' ም የሚበላ ፍለጋ ከቤቱ ወጥቶ ነበር።

ከዛ ምን ተፈጠረ?

ከኡሙ ማዕበድ ጋር

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ከሳሂባቸው አባበክር እና ከሁለቱ መንገድ ጠቋሚያቸው ጋር ሆነው ወደ ቤቱ ዘልቀው የሚበላ ካለ ጠየቁ። ኡሙ ማዕበድ ያሉበትን ከባድ ሁኔታ አስረዳቻቸው! በጣም ከሲታ፤ ወተት የማታወጣ ፍየል ብቻ እንዳለቻቸው ነገረቻቸው። ውዱ ነብያችን ﷺ አምጪያት ብለው ቢስሚላህ ብለው አለብዋት። ወዲያውም ብዛት ያለው ወተትን ሰጠች። የወተት ማጠራቀሚያውን ፀሞላ ጀመር! ሁሉም አስኪጠግቡ ጠጡ!

የዚህን ጊዜ ኡሙ ማዕበድ "አናንተ ግን ማናችሁ? ስማችሁ ማነው" ብላ ጠየቀች! ረሱለላህ ፡ ም ﷺ "አብዱላህ ፡ የአላህ ባሪያ" አልዋት። ከዛም አመስግነዋት ከድንኳኗ ወጥተው ጉዟቸውን ቀጠሉ!

ከዚህ ሁሉ አስደናቂ ክስተት በኃላ ባልዋ አቡ ማዕበድ መጣ! ቤቱ ውስጥ የሞላውን ወተት ሲመለከት በአግራሞት ጠየቀ። ምን ተፈጥሮ ነው ሲላት እንዲህ አለች ፡ እንድ የተባረከ መልካም ሰው በድንኳናችን አልፎ ነበር ብላ ሁኔታውን ተናገረች! ባልዋም አስኪ ስለሱ ግለጪልኝ አላት። ኡሙ ማዕበድ ፡ ም በሲራ ውስጥ ልናገኝ ከምንችለው ሁሉ የበለጠ አድግ ውብ የሆነ ገለጻዋን ጀመረች!

አለችም ፡

رأيت رجلا ظاهر الوضاءة, حسن الخلق, مليح الوجه . . .

«ንፅሕናው እና ጥራቱ ጉልህ የሆነ ሰው ተመለከትኩ! ፊቱ ያበራል። ከፍጥረቱ ሁሉ ውብ ነው። ወደፊት ወጣ ያለ ሆድ የለውም፤ አነስ ያለ ጭንቅላትም አልነበረውም። ቆንጆ ነበር! የተሟላ የተስተካከለ ፊት አለው። አዩኖቹ በጣም ጥልቅ እና ሰፊ ናቸው! ሽፋሽፍቶቹ ረጅም ናቸው! ድምፁ የተረጋጋ እና ጥርት ያለ ነበር። የአይኖቹ ነጮች በጣም የነጡ፤ ጥቁሩም በጣም ጥቁር ነበር ። ቅንድቦቹ ጥቅጥቅ ያሉ፤ ሲጋጠሙ የደረሱ ግን ያልተጋጠሙ ነበሩ። አንገታቸው ረጅም፤ ፀጉራቸውም በጣም ጥቁር ነበር!

إذا صمت فعليه الوقار, وإذا تكلم سما وعلاه البهاء

. . . . ዝም ሲል የክብር መንፈስ ይከበዋል፤ ሲናገር ደግሞ ብርሃን ከውስጡ የሚወጣ ይመስላል።

ንግግሩ ቆንጆ እና ጣፋጭ ነው። አጭር አልነበረም፤ ረጅምም አልነበረም! ይልቁኑ ንግግሩ ልክ ሀብል ላይ እንዳለ ጨሌ የተደረደረ ነበር ።

أجمل الناس وأبهاهم من بعيد, وأحسنه وأحلاه من قريب

. . . . ከሩቅ ሲመለከቱት በጣም ውብ እና የሚማርክ ሰው ነው። ሲቀርቡት የበለጠ ውብ እና የሚማርክ ነው።

ቀመቱ ለአይን አያስቸግርም። ከሁሉም (ከሶስቱ ሰዎች) የሚያበራው እና ላቅ ያለ ክብር የሚሰጠው አሱ ነው! ባልደረቦቹ ከበውት ይቀመጣሉ!

إن قال استمعوا لقوله, وإن أمر تبادروا إلى أمره

. . . . ሲናገር ሁሉም በትኩረት ያዳምጣሉ፤ ሲያዛቸው ደግሞ ትዕዛዙን ለመቀበል ፈጣን ናቸው። ከሱ በፊትም ሆነ በኃላ እንደሱ አይነት ሰው አላየሁም!» . . . በማለት ውብ የሆነውን ገለጻዋን አሰፈረች!

CamScanner

አጂብብብብ . . . ከውዱ መልዕክተኛ ﷺ ጋር የነበራት የትንሽ ጊዜ ቆይታ ይህንን አስባላት! ከቶ እንዴት አድርጎ ቢኸልቃቸው ነው?

ባልዋ ' ም : "ወላሂ ይህ ሰው የቁረይሽ ህዝብ አያወራለት ያለው ሰው ነው! አኔም ብቀላቀለው ደስ ይለኛል!" አለ

ረሱሊ ﷺ ከኡሙ ማዕበድ ቤት ወጥተው ወደ መዲና ጉዟቸውን በመቀጠል ላይ አያሉ መካ ላይ ከየት አና ማን እንዳለው የማይታወቅ አንድ ድምፅ ይሰማል! በግጥም መልክ ነበር የተወራው። የመካ ሰዎች ከውስጣቸው ባወጡት ትልቅ ሰው ማዘን እንዳለባቸው የሚያሳይ አና ለማረጋገጥ ኡሙ ማዕበድ ' ን አና ከሳሳው ፍየልዋን ቢጠይቁ ለሙሐመድ ﷺ እንደሚመሰክሩ የሚያሳይ ውብ ግጥም ነበር የተሰማው!

****

جزى الله رب الناس خير جزائه * رفيقين حلا خيمتي أم معبد
هما نزلا بالبر وارتحلا به * فأفلح من أمسى رفيق محمد
فيال قصي ما زوى الله عنكم * به من فعال لا تجازى وسؤدد
سلوا أختكم عن شاتها وإنائها * فإنكموا إن تسألوا الشاة تشهد
دعاها بشاة حائل فتحلبت * له بصريح ضرة الشاة مزبد
فغادره رهنا لديها لحالب * يدر لها في مصدر ثم مورد

****

ከቆይታ በኃላ ኡሙ ማዕበድ አና ባልዋ ረሱለላህ ' ን ﷺ መዲና ላይ ሄደው እንደተቀበሉ ይነገራል። ኢብኑ ሐጀር እንድ ኪታባቸው ላይ እንዲህ ይላሉ : "ረሱለላህ ﷺ ቢስሚላህ ብለው ወተቱን ያወጡለት ፍየል ምን ተፈጠረባት ልትሉ ትችላላችሁ! በሐቢቢ ﷺ እጅ የተባረከችው ፍየል የራማዳ አመት ላይ ማለትም (ሂጅራ ካደረጉ ከአስራ ስምንት አመት በኃላ) አስክትደርስ አና አስክትሞት ድረስ ወተት አየሰጠች ነበር በማለት ይናገራሉ! ሱብሃነላህ! . . . ረሱሊ ' ኮ ﷺ አርሶ የነኩት ነገር ሁሉ እኮ መድሐኒት ነው። በረካ ነው! አልሃምዱሊላህ ያንቱ ላደረገን!

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ በሒጅራ ጉዟቸው ላይ ብዙ የሚገርሙ ክስተቶችን አይተዋል፤ አስተናግደዋል። ከኡሙ ማዕበድ ቤት ከወጡ በኃላ ወደ መዲና መቅረብ ጀመሩ! መሸቷል፤ ደክሚቶዋል። በዚህም ወቅት 70 ሰዎችን የያዘ ጎሳ ያረፈበትን ድንኳን ይመለከታሉ። የጎሳው መሪ የሆነው ቡረይዳ ኢብን አል ሁሰይብ በዛ ማታ ወደ ድንኳናቸው የሚመጡትን ሰዎች ማንነታቸው ለማረጋገጥ ወደ ረሱለላህ ﷺ መጓዝ ጀመረ!

ሸፊዒ ﷺ ጋር ሲደርስ ግን እሱ ሳይጠይቃቸው አስቀድመው "ማን ነህ አንተ?" ብለው ጠየቁት! እሱም "ቡረይዳ" አባላለሁ አላቸው። ረሱሉ'ም ﷺ ወደ አባበክር ዞረው እንዲህ አሉ: "ያ አባበክር! በረደ አምሩና: አባበክር ሆዩ! አሁን ጉዳያችን ቀዘቀዘ!" አሉት። ቡረይዳ የሚለውን ስም በመጠቀም በሁኔታው የተፈጠረውን ግራ የመጋባት ስሜት ለማብረድ ተጠቀሙት። ያ ረሱለላህ! ከቶ እንዴት አድርጎ ቢኸልቆት ነው ወዱዱ?!

የዚህን ጊዜ ተራው የቡረይዳ ነበርና ማንነታቸውን ይጠይቃቸዋል። . . . የአላህ መልዕክተኛ ﷺ የመካ ስደተኛ እንደመሆናቸው እና ሙሽሪኮች እየፈለግዋቸው እንደመሆኑ አራሳቸውን ለመግለፅ ቅንጣት አልፈሩም፤ አላንገራገሩም'ም! "ሙሐመድ ኢብኑ አብዱላህ አላህ የላከኝ መልዕክተኛ ነኝ!" አሉት። ለኡሙ ማዕበድ ማንነታቸውን ሳይገልፁ የወጡት ነብዩ ለቡረይዳ ገለፁለት። ስለ እስልምናም ሰበኩት! በእንደዚህ ሁኔታ ሳይ ሆነውም ዳዕዋ ከማድረግ ወደኃላ አላሉም። የኔ ነብዩ ﷺ

ቡረይዳ ወዲያውኑ እስልምናን ተቀበለ። ሰባ የሚሆኑት ተከታዬቹም አብረውት ሰለሙ። በቅፅበቶች ውስጥ ሰሐባዎች ሆኑ። በሒጅራው ጉዞ ሳዩ ጓደኛቸው አባበክር እና ሁለቱ መንገድ ጠቋሚያቸውን በሚገርም ክስተት ቡረይዳ እና ሰዎቹ ተቀላቀልዋቸው። መዲና መግቢያ ሳዩ እስኪደርሱ ከበረካቸው እየተቋደሱ አብረዋቸው ተጓዙ። ቡረይዳ እና ሰዎቹ በሰአቱ መዲና መግባት ስለማይችሉ ቡረይዳ ጥምጣሙን አውልቆ ለሸፊዒ ﷺ ሰጣቸው! በቅርቡ እንደሚቀላቀልዋቸው ቃል ገብተውላቸው ተለያዩ። ከዛም ከኡሁድ በኃላ እንደተቀላቀልዋቸው ይነገራል። የረሱለላህ ﷺ ታማኝ ሰላይ እንደሆነ እና የፈትህ መካ ጊዜ እንደ ጦልሓ ጦሩን ፊት ለፊት በመምራት ባንዲራዎቹን ይዘው ወደ መካ ከገቡት መካከል እንደሆነም ይነገራል። ሱብሃነላህ

የሒጅራው ጉዞ የሚገርም ነው! የእምነት መንገድ እንዲህ ነው። አላህ የባረከው መንገድ ሁሉ የተቀደሰ ነው! ሒጅራ ቢነገር የማይጠገብ ድንቅ ጉዞ ነው! በቦታው የነበርኩ አስኪመስለኝ ድረስ ባነበብኩትና በሰማሁት ቁጥር ይነዝረኛል። ከዚህ ሁሉ ክስተት በኃላ የአላህ መልዕክተኛ አሳቸውን በመናፈቅ ቁባ ሳይ ሆነው የሚጠብቋቸውን ሙሐጂሮችና አንሳሮች ተቀላቀሉ።

አዲስ ማህበረሰብ! አዲስ ሐይል! ውብ ታሪክ'ን ሊፅፉ ወደ መዲና ዘለቁ!

የዛሒድ ኢቀባል'ን ግጥም አዚህ ጋር ልዋስ

የትውልድ ክፋት የነበረ፤
ጭቆና ቀንበር ተሰበረ።
ባሪያውም ከሰው ተቆጠረ፣
ወንድሜ መባል ተጀመረ፣
የፍቅር መሰረት ተኖረ።

የአላህ ሰላትና ሰላም በውዱ መልዕክተኛችን ﷺ ላይ ይውረድ!

هجرة النبي الى المدينة


አላህ ለረሱለላህ ﷺ ይህንን የኢማን መንገድ
ሲመርጥላቸው የሚጠብቃቸውን ማህበረሰብና
የሚጀምሩትን አዲስ ህይወት ባርኮላቸው ነው::
ሒጅራ የለውጥ ብሎም የድል መንገድ ነውና!
እኛስ መንገዳችንን
ለይተን ይሆን?...